# የሴቶች ዐምድ

## የሴቶች ሐዋርያነት



ክርስቶስ ከተነሣ በኋላ ከሁሉ በፊት ያየችው መግደላዊት ማርያም ናት

ጌታችን ኢየሱስ ለረዥም ዘመን በጭ
ቆና ቀንበር ይኖሩ የነበሩትን ሴቶች ከ
ጭቆና አላቆ እኩልነታቸውን ያከበረ
መሆኑ የማይታበል ሐቅ ቢሆንም ብዙ
ሰዎች የሴቶች ሐዋርያነት ከትንሣኤው
በኋላ እንጂ በፊት እንዳልነበር በማስመ
ሰል የሚናገሩ ጥቂቶች አይደሉም ።
ይሁን እንጂ ቅዱሳት መጻሕፍትን ስ
ንመለከት ደግሞ ከትንሣኤው በፊት ብ
ዙ ሴቶች ሐዋርያት እንደነበሩ ተጽፎ
እናገኛለን ።

ለምሳሌ ሳምራዊቷን ሴት ብንወስድ
ቁም ነገረኛ ወንጌላዊት እንደሆነች በ
መልእክቷ እናረጋግጣለን ። በሉቃስ ወ
ንጌል በምእራፍ 8 ላይም ብዙ ሴቶች ይ



www.ethiopianorthodox.org

ሴቶች ሐዋርያት ያላመኑትን በማስተማር እንዳሳሙኑ ትንቢት በመናገርና በዲቁና ሥራ ሳይቀር እንዳገለገሉ እሙን ነው ።

አንዳንድ ስለ ክርስትና እምነት ጠለቅ ያለ ትምህርትና እምነት የሌላቸው ሰዎች የክርስትና እምነት ሴቶችን የሚጨቁን በማስመሰል አንዳንድ ጥራዝ ነጠቅ ጥቅሶችን እየጠቃቀሱ ወጣት ሴቶች ከቤተ ክርስቲያን እንዲርቁ የሚያደርጉ ግለሰቦች አይጠፉም ።

ነገር ግን የተጠቀሱትን ጥቅሶች ስንመረምር የክርስትና እምነት ስለ ሰዎች ልጆች እኩልነት የሚናገርና የሚያንጸባርቅ ሃይማኖት ሆኖ እናገኘዋለን እንጂ ሴቶች እንዲጨቆኑ አያደርግም ስለዚህ በሃገርና በሃይማኖት ቀልድ የለምና ግለሰቦች ጥራዝ ነጠቅ አነጋገራቸውን እንዲያርሙ እንጠይቃለን ።

በተረፈ ሰውንና እግዚአብሔርን በሚያገናኘው መንገድ መራመድና ለሌሎቹም ቀናውን ጐዳና ማሳየት የሚኖርባቸው የወንዶች ሐዋርያት ብቻ ሳይሆኑ የሴቶች ሐዋርያትም እንደሆኑ በላይ ከሞላ ጐደል ከጠቆምናቸው ማስረጃዎች ልንረዳ እንችላለን እግዚአብሔር የሚመለከተው ልባችንን እንጂ ፆታችንን አይደለም ።

ስለዚህ ሥራችን አነጋገራችን አስተሳሰባችን ከክርስቶስ ሥርዓት ጋር የሚስማማ መሆን አለበት ክርስቶስ እንዲረዳን ከፈለግን ከጉድለታችን መታረም አለብን ። ቃሉ "ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉም " ይላል እውነትም ያለ እርሱ ምንም ማድረግ አንችልም ። እንግዲያውስ እርሱን አማካሪያችን አድርገን ያለ ምንም የፆታ ልዩነት ከእርሱ በተማርነው መሠረት እውነተኞች ሐዋርያት እንሁን ።

ድንጋይና ጭቃ ቢቀጣጠሉ ታላቅ ቤት ረጅም ቅጥር ይሆናሉ እናንተም መሬታውያን ሰዎች እንደዚህ ብትረዳዱ ጥበባችሁና ኃይላችሁ ከሰማይ በደረሰ ተብሎ እንደተጻፈው ሁሉ እኛም ጥበባችንና ኃይላችን ከፍ ያለ እንዲሆን ወንድ ሴት ቄስ ዲያቆን ብለን ሳንለይ ሁላችንም የሚፈለግብንን ግዳጅ ከፈፀምን ለቤተ ክርስቲያናችን ኩራትና ብልጽግና ለሌላውም አርዓያ ልንሆን እንችላለን ።

የምሳሌ መጽሐፍ እንዲህ ይላል፡- እናንተ ሰነፎች ድንቁርናን ከማይመለስ በት ሽጡት የሰነበተ እንደሆነ ሁልጊዜ ያው ይመስለዋልና ።

በዚህ ጥቅስ መሠረት ስንፍና ስንፍናችንን አይቶ ተንሰራርቶ እንዳይቀመጥ በሕብረት በፍቅር ያለ ነቀፌታ ያለ ፆታ ልዩነት ለመሥራት ተባብረን እንነሳ የሴቶች ሐዋርያነት ከትላንትና በስቲያ የተጀመረ ትላንትና የነበረ ዛሬ ያከተመ ሳይሆን ከክርስቶስ ልደት ጀምሮ በየጊዜው ብዙ የሴቶች ሐዋርያት እንደ ነበሩ መጽሐፉ ያስረዳል ። ዛሬም ቢሆን ሃሳባችንን በሙሉ ለእርሱ ብናስረክብ እግዚአብሔር በብዙ መንገድ ሊጠቀምብን እንደሚችል ማወቅ አለብን ። እግዚአብሔር ለሥራው የሚመርጣቸው ሰዎች ወንዶች ብቻ ወይንም ደግሞ አፈ ጮሌዎች የሆኑትን ሳይሆን ቃሌን በከናፍራቸው ላስተላልፍ እችላለሁን ? እኔን ሊወክሉ ከእኔ ለመማር ትሁታን ናቸውን? በማለት ስለሚጠይቅ የእርሱን ቃል በእውነት ተቀብለው እውነተኞች ሐዋርያት የሚሆኑትን ነው ።

ስለዚህም ራሱ ክርስቶስ ተገልጾ የተናገራቸውና ፍቅሩንም የገለጸላቸው ሴቶች በጊዜው የነበረውን የአይሁድን ቁጣ ሳይፈሩ ወንዶች ደቀ መዛሙርቱ ሳይሄዱ እነእርሱ ገስግሰው ሄደው ከመቃብሩ አጠገብ ተዘዋውረው ይፈልጉት ለነበሩትና በትህትና ከእርሱ ተምረው በእውነት ማስተላለፍ ለሚችሉት ሴቶች ሐዋርያት ነበር ።

በዚህም መሠረት በሃገራችን እናቶችም የእነርሱን ፈለግ በመከተል በሐዋርያነት በጉልበታቸው ፣ በገንዘባቸውና በሃሳባቸው ቤተ ክርስቲያንን ሲያገለግሉ ቆይተዋል አሁንም በማገልገል ላይ ናቸው ።

ለዚህም ማስረጃ ቢያስፈልግ በየ አብያተ ክርስቲያናቱ ዙሪያ በየጊዜው ጡዋፉን ፣ ዘቢቡን ፣ መባኡንና በጠቅላላ ለቤተ ክርስቲያኒቱ የሚያስፈልጋትን ሁሉ ይዘው የሚጐርፉት የሴቶችን ብዛት መመልከት ነው ።

እንግዲያውስ እኛም ወጣት ክርስቲያን ሴቶች የእናቶቻችንን አርዓያ በመከተል እውነተኞች ሐዋርያት ለመሆን በቃሉ የማናፍር ከሆነ ለክርስቲያን ሴቶች የውይይት ዓምድ እንዲሆን ታስቦ የሴቶች ዐምድ ተብሎ በዚሁ መጽሔት ስለተከፈተ ጥያቄአችንንም ሆነ ትምህርታችንን እየጻፍን ለዚህ ዐምድ አዘጋጅ እንድንልክ ተጋብዘናል ለእውነተኛውና ከእንቅልፍ እንደሚነቃ ለተነሣው እግዚአብሔርም በቃሉ ሳናፍር እንደቀደሙት እናቶች በሐዋርያነት እንድናገለግለው ተጠርተናል ጥሪውን አክብረን ዛሬውኑ ለመገኘት እንዘጋጅ የዝግጅት ቀን ዛሬ እንጂ ነገ አይደለምና ።

ብርሃን ተድላ



ትንሣኤ ቁጥር 19 መጋቢት 1971

www.ethiopianorthodox.org